# የACPS Express 2/17/2023: የፌብሩዋሪ (February)፣ ተማሪን እና ሠራተኛን - እውቅና-መስጠት

## የፌብሩዋሪ (February)፣ ተማሪን እና ሠራተኛን - እውቅና-መስጠት




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) አስተማሪዎች እና ተማሪዎች፤ ያላቸውን-ጊዜ በዋነኛነት-እንዲቀመጡ ያደረጋቸውን ቦታ በፌብሩዋሪ (February) ወር ውስጥ አግኝተዋል። ስኬታማነታቸውን በማክበራችን፤ ኩራት ይሠማናል።

### በቨርጂኒያ አጠቃላይ ስብሰባ (General Assembly) ላይ፣ ለርዕሰ-መምህር ምስጋና-ቀረበ



የላየልስ-ክራውች ትራድሽናል አካዳሚ (Lyles-Crouch Traditional Academy/(Lyles-Crouch) ርዕሰ-መምህር ዶ/ር ፓትሪሲአ ዚሲኦስ (Dr. Patricia Zissios)- በቨርጅኒያ አጠቃላይ ስብሰባ (General Assembly) በተደረገበት - በጄንዋሪ (Jan.) 23 ቀን 2023 ላይ - እንደ ትምህርት-ሰጪ እና የትምህርት ቤት አስተዳደር ሆነው ለአምስት አስርት-ዓመታት በማገልገላቸው - እውቅናን-አግኝተዋል።

“ራዕያቸው እና ትጋታቸው - በከተማው ውስጥ፣ ከኮመንዌልዝ/Commonwealth እና ከሃገሪቱ - ውጤታ ከሆኑ ትምህርት ቤቶች መካከል፣ ላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) አንደኛው እንዲሆን የመሩ-ናቸው፣” ብለዋል - ልዑክ ኤሊዛቤት ቤኔት-ፓርከር (Delegate Elizabeth Bennett-Parker) ሲናገሩ። “ለመማር ባላት-የጋለ ስሜት፣ ተቆጥረው-የማያልቁ ሕይወቶችን የነካች ናት። ከትውልድ-ወደ ትውልድ የመጡ ተማሪዎችን - በትምህርታቸው እና በስራ-መስኮቻቸው ላይ አስፈላጊ-የሆነውን ውጤት-ያለው ስኬት እንዲያገኙ መሣሪያዎች/tools እና እርዳታን የሚሰጡ-ናቸው።”

ዶ/ር ዚሲኦስ (Dr. Zissios)፣ ላበረከቱት በርካታ ውጤማ-ስኬቶች፤ በ‘House Joint Resolution No. 554’ ውስጥ ክብርን-ያገኙም ናቸው። የ2012-14 ‘National School of Character’ ሽልማትን፣ በጠቅላላ የልጅ እድገት-ላይ ትኩረትን በማሳየታቸው፣ ከ‘Character Education Partnership’ - ላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) እንዲያገኝ የረዱ-ናቸው። እንደ የቨርጅኒያ የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራን ማኅበር (Virginia Association of Elementary School Principals)

የቦርድ-አባልነታቸው፤ ዶ/ር ዚሲኦስ (Dr. Zissios) - የ‘2017 Don Lacey’ ሽልማትን - ለላቀ-ደረጃ፣ ለተማሪ ውጤታማ-ስኬት እና የትምህርት-አሰጣጥ አመራርነታቸው ላይ ላሳዩት የማይናወጥ ቁርጠኝነት - ሽልማቱን አግኝተዋል። ከሌሎች በርካታ ሽልማቶች እና ምስጋናዎች መካከልም - በ2009 ላይ - የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ-መምህር ሆነውም-ነበር።

በቨርጅኒያ ሕግ-ቀራጮች (Virginia lawmakers) - ዶ/ር ዚሲኦስ (Dr. Zissios) ይህን እውቅና-ስላገኙ፤ የላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) የወላጅ አስተማሪ ማኅበር (parent teacher association) ፕሬዚደንት የሆኑት ማቲአስ ፓላቨንሲኦ (Matias Palavecino) እንኳን-ደስ አለዎት ብለዋል። “ከዶ/ር ዚሲኦስ (Dr. Zissios) በበለጠ-ሁኔታ ይህ-ይገባዋል ብዬ የማስበው ሰው-የለም፣” ብለዋል። “ካላት የጋለ-ስሜት እና ትጋት ላይ፣ የበለጠ የማደንቀው አንድ-ነገር - ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች የምታሳየው ብቻ ሳይሆን፤ ነገር ግን ለማህበረሰቡም ጭምር የምታደርገውንም-ነው። የፒቲኤ (PTA) ህይወት፣ አስደሳች እና ዋጋ-የሚከፍል አድርጋዋለች።”

## የሠራተኛ-አባል የሆኑት፤ የመንገድ-ማቋረጫ መሪ (Crossing Guard) የምስጋና ሽልማት-አግኝተዋል




የቨርጅኒያ የመጓጓዣ መምሪያ (The Virginia Department of Transportation’s (VDOT) - ወደ ትምህርት ቤት በደህንነንት-መሄጃ መንገዶች (Safe Routes to School) ፕሮግራም፤ እንደ ቨርጅኒያ ከሁሉ-የላቀ ደረጃ ያላቸው የመንገድ-ማቋረጫ መሪ (Most Outstanding Crossing Guard) ሽልማትን እንዲቀበሉ፣ ካንዴንስ ዶራን (Candance Doran)ን መርጧል። ዶራን (Doran)፣ በፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት ቤት ካውንስለር ሲሆኑ፤ ከትምህርት ቤቱ የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ አጠገብ - የትራፊክ ፍሰቱን በመጠበቅ እና ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በደህንነት አውርደው እንዲሄዱ - በጠዋት እና በከሰዓት በኋላ የመንገድ-ማቋረጥ ስራዎችን ያከናውናሉ።

“ሚስ ዶራን (Ms. Doran)፣ በነቃ-ህሊና የሚሰሩ እና አስተማማኝ-ናቸው፤” ብለዋል የፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) ርዕሰ-መምህር ራቼል ዲስክነር (Rachael Dischner)። “በተጨማሪነት የተሰጣትን ስራ በደንብ-የምታከናውን እና ሁሉጊዜ ስራዋን በፈገግታ የምትሰራ-ናት።”

‘VDOT’፤ ጥቂት-የመንገድ ማቋረጫ መሪዎችን - ተማሪዎች በደህንነት እንዲያቋርጡ ለሚያሳዩት ትጋት - በዚህ-ዓመት፣ በማቋረጫ-መሪን ማመስገኛ ቀን በነበረው - በፌብሩዋሪ (Feb.) 8 ቀን ላይ፤ ክብር-ሰጥቷል። አሸናፊዎቹ፤ ሰርተፊኬት እና ስጦታን አግኝተዋል።

## የACHS - ‘We the People’ ቡድን፣ የ‘Best Unit 2’ ሽልማትን - በስቴት/State የመጨረሻ-ጨዋታ ላይ አሸንፈው-አግኝተዋል



የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS)፣ ‘We the People’ ቡድን - በ‘University of Virginia Darden School of Business’ ውስጥ በተካሄደው - የስቴት/State የመጨረሻ-ጨዋታ፣ በጄንዋሪ (Jan.) 28, 2023 ላይ - የ‘Best Unit 2’ ሽልማትን አሸንፏል። የ‘The congressional mock hearing’ ውድድር - በስድስት የጥናት ክፍሎች ውስጥ በ‘Center for Civic Education’ በተቀረጸው-ውስጥ፣ ተፈትነዋል።

ጥያቄዎቹ፤ ከፊሎሶፊያዊ እስከ ታሪካዊ መሠረቶች በሆነው በአሜሪካ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ባካተተ-ስፋት ውስጥ፣ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን የአሜርካ የሕገ-መንግስታዊ ዲሞክራዊ ምን-ዓይነት ፈተና ሊገጥመው እንደሚችል አካትቶ-ይዞ ነበር። ቢጀ ብሮክ (JB Brock)፣ ቲግራን ሲሴ (Tigran Ceesay)፣ ማሊክ ኩናታ (Malik Kunata) እና ሚካህ ስትዋርት (Micah Stewart)፤ በ‘Best Unit 2’ ሽልማት ውስጥ - ለእነርሱ መከላከያ-ነጥባቸው አድርገው በ"How Did the Framers Create the Constitution?” ከሚለው ጋር ተያያዥ በሆነ - ሽልማታቸውን አግኝተዋል።

“የ‘We the People’ ፕሮግራም - ጠንካራ-የሆነ ነገር ግን ከሚገባው-በላይ የልፋትን-ዋጋ በሚከፍል ሁኔታ ጥልቅ ጥናትን በስድስት ክፍሎች - በክልላዊ እና ስቴት-አቀፍ ውድድሮች ውስጥ የተውጣጣ ነው” ብለዋል ራ አሊም ሻባዝ (Ra Alim Shabazz) - የACHS የኅብረ ትምህርት/social studies አስተማሪ። “በአንድነት-አብረው ከመጡ የተማሪ ቡድኖች፣ እና ቤተሰቦች በአንድ-ዓይነት የተሰባሰበውን ግብ መቅሰሚያ-ሆኖ ለአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) በሚችሉት ተመራጭ የሆነ የመሰባሰብ አቅምን የወከሉትን፤ በበለጠ-ሁኔታ ኩራት-ሊሰጠኝ የቻለ ነገር የለም። እነርሱ ሃሳቡን በእውነት ያካተቱ ሲሆን፣ በህገ-መንግስቱ ላይ የላቀ-ደረጃ ያለው እና እውቀትን በማዳበር መግባት እና ተፈጻሚነቱን ከማሳካት-ጋር መስራት፤ ዋጋ-ያለው ግብ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለራሳቸው የግል ነፃነት ቁልፍም-ነው።”

## የ‘ACHS’ የኮራል ዳይሬክተር፤ ‘40 Under 40’ ተሰይሟል



የ'ኮራል እንቅስቃሴ/Choral Activities ዳይሬክተር የሆኑት፤ ቴዎዶር ቶርፔ (Theodore Thorpe) III  - ከ2023 Yamaha 40 Under 40 Excellence in Music Education ክብርን-ካገኙት ውስጥ አንዱ-ናቸው። የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - ትምህርት-ሰጪ፤ የዲስፕሊን እና የስራ-ስነ ምግባር (work ethic)ን ጠቃሚነት በውስጣቸው-በመትከት - ተማሪዎች ኃይል-እንዲሰማቸው-አድርገዋል። እንደ ኮንዳክተር፣ ትምህርት-ሰጪ እና የሙዚቃ ዳይሬክነት - ከሆነው የስራ-ሚናቸው በተጨማሪ፤ ቶርፔ (Thorpe) በተጨማሪም፤ ድምፃዊ፣ ኮምፖዘር፣ አዘጋጅ እና ፒያኖ-ተጫዋች ናቸው። በፌብሩዋሪ (Feb.) 4 ቀን 2023፤ በ "Saturday Night Live" ላይ፣ ቶርፔ (Thorpe) - 'Coldplay'ን በባንድ አቀራረቡ ላይ አብረው-ተገኝተዋል።

ቶርፔ (Thorpe) መጀመሪያ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) 13 ዓመታት በፊት የመጣ፣ እና በከፍተኛ-ደረጃ ኮራል/choral ፕሮግራም ውስጥ - 30 ተማሪዎች ብቻ ነበሩት። በሁለት ዓመታት ውስጥ፤ ፕሮግራሙ ወደ 100 ተማሪዎች አድጓል።  የእርሳቸው የመዘምራን-ቡድን (choir) በአሁኑ-ጊዜ - ረጅም ዝርዝር ያለው አስደናቂ ዝግጅቶችን-ያቀረበ ሲሆን፤ በ2016 የ'National Museum of African American History and Culture' ሚውዚየም ተመርቆ-በተከፈተ ጊዜ እና በ2017፣ Virginia Music Educators Association Conference የመዘምራን-ቡድን (choir) አቀራረብን ያካተተውን አከናውኗል። በተጨማሪም፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመዘምራን-ቡድን (choir) - በቴሊቪዝን በተሰራጨ ዝግጅቶች ላይ በKennedy Center Honors እና Christmas in Washington አቅርቦ-ነበር።

'Yamaha'፤ የ"40 Under 40" የሙዚቃ ትምህርት አድቮኬሲ ፕሮግራም በ2021 ላይ ያስጀመረ ሲሆን፤ የሙዚቃ ፕሮግራሞችን በማሳደግ እና በማጠናከር ላይ ልዩነትን-የፈጠሩን ግሩም-የሆኑ የሙዚቃ ትምህርት-ሰጪዎችን እውቅና-ለመስጠትና ለማክበር የተዘጋጀ-ነው። በ2023 ውስጥ ክብር-ያገኙት ትምህርት-ሰጪዎች፤ ከCOVID-19 ወረርሽን በፊት፣ በነበረበት-ወቅት እና በኋላ እየበለጸጉ በመቀጠል የመስራት-ችሎታቸው - እና የሙዚቃ ፕሮግራሞቻቸው እንዲበለጽግ በመጠበቃቸው ተመስግነዋል። ይህ ቡድን፤ ፈጠራዊ እና ሃሳባዊ መፍትሄዎችን በመፍጠር - አዲስ እና ትልቅ ሃሳቦችን ለማስፈጸም ላይ እየሰሩ ባሉበት ጊዜ ላይ ሆነው፤ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰቦች ውስጥ የሙዚቃ ትምህርት እንዲያድግ እና እንዲሻሻል ሰርተዋል።

## የ‘ACHS Ceramics Student’፣ በፌርፋክስ ካውንቲ (Fairfax County) ክልል የ‘Scholastic Art’ ሽልማቶች ላይ - የብር ቁልፍ/Silver Keyን አግኝተዋል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ጁኒየር/junior - ካሊና ከፍማን (Kalina Kaufmann)፤ በፌርፋክስ ካውንቲ (Fairfax County) ክልል የ‘Scholastic Art’ ሽልማቶች ላይ - ላቀረበችን የሴራሚክ ቅርጽ (ceramic sculpture)፣ የብር ቁልፍ/Silver Keyን አግኝታለች። ውድድሩ፤ 395 ተማሪዎችን እውቅና-የሰጠ ሆኖ፣ የላቀ-ደረጃ ላላቸው የስዕል ስራዎች 629 ሽልማቶች ነበሩት። ተካፋዮች የነበሩት፤ ከ7-12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የአሌክሳንድርያ፣ የፌርፋክስ ከተማ፣ የፌርፋክስ (Fairfax)-እና የፎልስ-ቸርች (Falls Church) ካውንቲን የመጡን ያካተተ-ነበር። የስዕል ስራዎች - ገብተው የነበሩት እና ዳኝንነት የተሰጣቸው የነበሩት በየምድቦቻቸው ሲሆን፣ ይህም የሚያካትተው፤ ስዕል መሣል/drawing፣ የቀለም-ቅብ/painting፣ የሕትመት-ስራ/printmaking፣ በፎተግራፍ-ስራ፣ በሴራሚክስ/ceramics፣ ቅርፃ-ቅርጽ/sculpture፣ ዲጂታል አርት/digital art፣ ዲዛይን፣ አርክቴክቸር፣ ጌጣጌጥ-ስራ፣ በፋሽን፣ በፊልም እና በአኒሜሽን/animation፣ በሚክስድ ሚዲያ እና የአርት ፖትፎሊዮዎች (mixed media and art portfolios)ን ያካተተ-ነበር።

የወርቅ/Gold እና የብር ቁልፍ/Silver Key የስዕል-ስራዎቹ፤ በ‘Northern Virginia Community College’ - በ‘Annandale Campus’ Ernst Community Cultural Center’፤ ውስጥ እስከ ሐሙስ ማርች (March) 23 ቀን 2023 ድረስ ለይታ-ቀርቦ የሚቆይ ይሆናል። የሽልማቶች ስነ-ስርዓቱ፣ ሮብ፣ ማርች (March) 1 ቀን 2023 ላይ ይከናወናል።

የ‘The Scholastic Art’ የሽልማት ፕሮግራም — በ‘Alliance for Young Artists and Writers’ የቀረበና — ትልቁ፣ ለረጅም-ጊዜ እውቅና-አድርጎ የተካሄድ ፕሮግራም ሆኖ በአሜሪካ ውስጥ በ1923 የተመሰረተ እና ለ10 ዓመታት ሲከበር-የነበረ፣ ሽልማቶቹ ለወጣት-ታዳጊዎች - በሃገራችን በይበልጥ ክብር አግኝተው የተከበሩ የስነ-ጥበብ-ባለሞያተሞች የሆኑን እውቅና-የሰጠ ነው።

## የ‘ACHS’ አትሌት - የ‘Gatorade Virginia Volleyball Player of the Year’ ሆነው ተሰይመዋል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ሲኒየር ሚላን ሬክስ (senior Milan Rex)፤ የ‘Gatorade Virginia የቮሊቦል/Volleyball’ የዓመቱ ምርጥ-ተጫዋች ናት። ሬክስ (Rex)፤ የ‘ACHS’ ተማሪ-አትሌት ሆና ይህን ክብር ስታገኝ፣ የመጀመሪያዋ ናት። ሽልማቱ - ሬክስ (Rex)ን እውቅና-የሰጠው፣ ጉልህ-ሆኖ ለታየው የአትሌቲክ የላቀ-ደረጃዋ እንዲሁም በቀለም ትምህርት ስኬታማ ውጤት ከፍተኛ-ደረጃን በመያዝ እና በመጫወቻ-ሜዳ ላይ እና ከዚያ-ውጪም ባለው ትጋቷ-ምሳሌነቷን በማድነቅ-ነው። እነዚህ የመገለጫ ባህሪያቶች፤ ሬክስ (Rex)ን እንደ የቨርጅኒያ ግሩም-የሆነች የቮሊቦል ተጫዋች (volleyball player) አድርጎ ለይቶ-ያወጣታል።

የ5-foot-11-inch ቁመት ያላት ሲኒየር - ቲንታኖች (Titans) 32-2 ሬከርድ እና የ ‘Class 6 State Championship’ን በዚህ ባለፈው ሲዝን/season፤ መምራት የቻለች-ናት። ሬክስ (Rex) - የ‘Class 6’ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች እና የአሜሪካ የቮሊቦል አሰልጣኞች ማህበር ሁለተኛ ቡድን - የ‘All-American selection’ ነበረች።

በተጨማሪም፤ ሬክስ (Rex) - የ4.46 GPA የጠበቀች እና በአካባቢው ለወጣት የቮሊቦች እና የቴኒስ አሰልጣኝነት የበጎ-ፈቃደኛ-ስራን ያበረከተች ናት። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ‘chapter of the National Honor Society’ እና የ‘National Charity League’s Port City Chapter’ በተካሄደበት ጊዜ፤ ጊዜዋን ለማህበረሰብ ተነሳሽነት የስራ-አገልግሎት በማዋል፤ የሠራችም-ናት። ሬክስ (Rex)፤ በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ - በሳንታ ባርባራ (Santa Barbara) ውስጥ - በዚህ በልግ (fall)፣ በስኮላርሽፕ የቮሊቦል ውስጥ ለመጫወት - ብሄራዊ ለማድረግ ቃል-መግቢያ ደብዳቤ (National Letter of Intent to play volleyball)ን ፈርማለች።

## ድምፃችሁን አጋሩ: ፍትሃዊ-እኩልነትን ማሳያ (Equity Climate) - የዳሰሳ-ጥናት፣ እስከ ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን 2023 ድረስ ክፍት-ነው






ሦስተኛው ዓመታዊ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) Equity for all Climate Survey እየተካሄደ፤ ወደ አጋማሽ-ደረጃው ላይ የደረሰበት ጊዜ ነው፤ ይህም እስከ ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን 2023 ድረስ-ክፍት ሆኖ መገኘት ይችላል። ይህ የዳሰሳ-ጥናት ማድረግ፤ ACPS ለሁሉም እኩል የሆነ የመማር አካባቢን ለማሳካት በሚያደርገው-ጥረት - ከ2025 Strategic Plan ጋር ከተቀመጡት-ግቦች ጋር ሆኖ ለማከናወን-ይረዳል።

ድምፃችሁ እንዴት ልዩነትን እንደሚያመጣ የበለጠ ለማወቅ፤ በሁለቱም በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ - ያሉትን ቪዲዮዎቻችንን ተመልከቷቸው።

የፍትሃዊ-እኩልነት (equity) የዳሰሳ-ጥናት፤ የተማሪ ስኬት-ላይ መድረስ ለማረጋገጥ ጠንክረን-በምንሰራበት ጊዜ፣ በመማር ላይ የሚኖሩ እንቅፋቶች ላይ ምላሽ-በመስጠት ቀጣይነት-ያለው ዓላማችን ውስጥ - ወሳኝ-የሆነ ክፍል አለው። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለሁሉም ከpreK-12 ቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍል/school division ውስጥ - በተማሪ መማር፣ በማህበራዊ ስሜታዊነት እርዳታ እና ደህንነት-ላይ ጨምሮ፣ ባሉት ነገሮች ዙሪያ፣ ያላቸውን አመለካከል-ለመስጠት ክፍት-ይሆናል።

የዳሰሳ-ጥናቱ፣ እስከ 30 የሚደርሱ ጥያቄዎች ጨምሮ፤ እና ሞልቶ-ለማጠናቀቅ፣ ከ10-15 ደቂቃዎችን የሚወስድ ይሆናል። ገለልተኛ-የሆነ፣ ሦስተኛ-ወገን የሆነ-ድርጅት - የዳሰሳ-ጥናቱን የሚያስተዳድር፣ እና ሁሉም ምላሾች በሚስጢራዊነት የሚያዙም ይሆናል። የዳሰሳ ጥናቱ፣ በኦንላይን፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በዳሪ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ይገኛል።

የዳሰሳ-ጥናቱን ለማጠናቀቅ እርዳታ-ለማግኘት፤ ጠቃሚ-የሆኑ ትዕዛዞችን የሚያሳየውን ቪዲዮዎች፣ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና በአረብኛ እባካችሁ ተመልከቱ።

## ለ‘Black History Month’ ስፖት-ላይት/Spotlight የሆነ ተማሪ: የ‘ACHS’ የ‘Black Student Union’




የ‘Black Student Union (BSU)’፤ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ ለውጥን ለመፍጠር - የጥቁር ተማሪ ድምጾችን ማጉላት የሚችል -ስብስብ-ያላቸውን ነሳቶችን የያዘ በንቃት-የሚሰራ ኃይል-ነው። የ‘BSU’ ፕሬዚዳንት - ሚራክል ግሮስ (Miracle Gross)፤ እነዚህ ቃላቶችን - ክለቡን ለመግለጽ ተጠቅመዋል። “እውነተኛ የሆነ እና ፀረ-ዘረኝነት ውይይቶች ለማድረግ - በቁርጠኝነት እንሰራለን።” ግሮስ (Gross) እንዳሉት፤ ‘BSU’ - እርምጃ-ለመውሰድ እና ስለ አፍሪካዊ አሜሪካዊያን ተሞክሮዎች፣ ታሪክ እና ባህል - የማህበራዊ ንቃተ-ህሊናን ለማሳደግ በትጋት-የሚሰራ በንቁ-ቅልጥፍና የሚሰሩ መሪዎችን - ለመገንባት ይመኛል። “በሁሉም ጥቁነት ውስጥ ያለውን ውበት እውቅና የምንሰጠው እና የምናደንቀው ነው፤ እና በውስጥ-ለውጥ የተያዘውን የዘረኝነት ሰንሰለትን እንሰባብራለን።

‘BSU’ - በ1967፣ በተማሪ አክቲቪስቶች - አሁንም በስራ-ላይ ካሉት እና ግንኙነት ካላቸው ጋር ባለው-ቡድን - የተመሰረተ-ነው። ክለቡ፤ በቅድመ 2000ዎቹ ውስጥ፣ በACHS ውስጥ ዳግም-የተመሰረተ ነበር። ከዚያን-ጊዜ ጀምሮ፤ ድርጅቱ የአሰራር-ፍጥነቱን አግኝቷል። ለጥቁር ተማሪዎች እና ለACHS ማህበረሰብ፣ እንደ ድጋፍ-ሰጪ እና ነጻብራቅ ፈጣሪ አካባቢን የሚያስገኝ ሆኖ የሚያገለግል-ነው። ስብሰባዎቹ የሚያካትተው፤ ሣምንታዊ ስብሰባዎችን፣ የዝግጅቶች እና የትምህርት ቤት አቀፍ የጥቁር ባህል አከባበሮችን፣ በተለይ ደግሞ በ‘Black History Month’ ወቅት የሚካሄድውን ያካትታል።

ክለቡ፤ በACHS ውስጥ ለሚገኙ ጥቁር ተማሪዎች - ሁሉን-ተቀባይ የሆነ ቦታ-ነው። የዘር አድልዎችን - በትምህርት ላይ ትኩረት በመስጠት አጣምሮ-እየተመለከተ፣ ለተማሪዎች ተጠሪ-ተከራካሪ ሆኖ ይሰራል። ግሮስ (Gross) ሲገልጹ፤ “BSU፣ በርካታ ርዕሶች ላይ - የአፍሪካዊ አፍሪካዊ አሜሪካዊያን ዳያስፖራን እንደ የዘረኝነት ታሪክ፣ ከትምህርት ቤት ወደ-እስር ቤት የሚያገናኝ ቱቦ፣ የባህል አግባብነት፣ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ትምህርት ለጥቁር ማህበረሰብ፣ ባህላዊ በዓላቶችን እና ሌሎችን-ጉዳዮች ላይ ምላሽ-የሚሰጥ ነው።”

“የተማሪ ድምጽ/student voice” - ኃይል-ያላቸው ስሜት እና የተሳታፊነት ስሜት እንዲኖር ወሳኝ-መሆኑን - ግሮስ (Gross) ያምናሉ። ‘BSU’ ዓላማ ያደረገው፤ ለጥቁር ተማሪዎች - ያላቸውን ተሞክሮዎች እንዲወያዩ ቦታን ማቅረብ-ነው። ተማሪዎች የሚሰማቸውን ትግል በድምጻቸው ማሰማት ያስፈልጋቸዋል፤ በተለይ-ደግሞ ዓለም-በአጠቃላይ የዘረኝነትን ሁኔታ እና አስከፊ የሆነ ወረርሽኝን እየተጋፈጠ-ባለበት ጊዜ፤ ብለዋል። “አንድ-ሰው የሚሰማውን የሚገልጽበት ሁኔታ ሳይኖረው ሲቀር፣ ክብደቡ በትከሻቻቸው ላይ መጠራቀም-እንደሚጀምር - ምንም ድብቅ-ነገር አይደለም። እና ይህን የሚገልጹበት ቦታ ስለሌላቸው፣ ምንም-መምሪያዎች ስለሌሉ፣ ወይም ምንም ደህንነቱ-የተጠበቀ ቦታ ስለሌለ፤ ያላቸውን ንዴት፣ መጎዳት እና ያላቸውን ሃዘን - የትምህርት ቤት ስርዓቱ ‘acting out’ ብሎ

በሚጠራው-መንገድ ለመግለጽ-ይሞክራሉ። ‘BSU’ እነዚህ ምላሽ-ሲያገኙ ማየት ይፈልጋል፤ ስለሆነም - ከትምህርት ቤት ወደ እስር-ቤት የሚጎትት ቱቦ ሆኖ እንዳይመራቸው ያደርጋል።

ግሮስ (Gross) እንዳሉት፤ የትኩረት ቡድን የክብ-ጠረጴዛ ውይይቶችን - ስለ ተማሪዎች ተሞክሮዎች በተመለከተ ወደ ዓለም እና ማህበራዊ ጉዳዮች ለማካተት ‘BSU’ ማካሄድ እንዳለበት ሃሳብ-ያቀርባል፤ ብለዋል። እንደዚህ ዓይነቶቹ የመግለጫ-ቦታዎች (outlet)፤ ተማሪዎች ያሏቸውን ተሞክሮዎች ለማጋራት እና ያላቸውን ስሜቶች ለመግለጽ እና በመማሪያ-ክፍላቸው ውስጥ ሲሆኑ በትምህርታቸው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ እንደሚረዳቸው ያምናሉ። በመጨመርም-ሲናገሩ፤ “በማቆያ-ቦታ ከመያዝ/detention ወይም ከማገድ/suspension ይልቅ - በአማራጭነት ያሉ የዲስፕሊን ዘዴዎች ላይ ከፍ-ያለ ትኩረት መስጠት-ከጀመርን፤ ተማሪዎችን በትምህርታቸው ላይ ለማቆየት እና ስኬታማ ለማድረግ ጉልህ-የሆነ መሻሻልን ለማግኘት የሚረዳን-ይሆናል።

የ2023 - የ‘Black History Month’ መግለጫ/theme የሆነው መቋቋም/resistance - ለ‘BSU’ የትውልድ-መስመሩን፣ ባህሉን እና ስኬቱን - አምቆ-ያቆየውን ትግል-ለመቋቋም ወደ ትኩረት ያመጣው-ነው። ግሮስ (Gross) ሲናገሩ፤ በዚህ ወር - ለዚያ ታሪክ መቀመጫ-ሆኖ የከፈለ - በ21ኛ ክፍለ-ዘመን ላይ እንቢ ብሎ የመቋቋም ሁኔታ መቀጠሉ ምን-ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ብርሃን የሆነን ጊዜ ነው። “የጥቁር ሰዎች፤ በተደጋጋሚ አሜሪካ ውስጥ የሚፈለግ - የነፃነት፣ የሊበርቲ (liberty) እና ፍትህ-ለሁሉም ዓላማ-አድርጎ መጓዝን ሲገፉበት ቆይተዋል።

የ‘BSU’ - የ‘Black History Month’ን በACHS ውስጥ በሚያከብር-ጊዜ - የጥቁርን የአልበገርነት እንቅስቃሴ ወይም ምስልን በምሳሌነት የሚገልጽ የተሸበረቀ ይዘት-ያለውን በር ያካተተ ነው። የ‘The Black Box Theatre’ በርካታ ይዘቶች ያላቸውን የጥቁር አልበገርባይነት የሚፈትሽ እና ተጋባዥ ተናጋሪ የሆኑትን - በቺካጎ፣ የ‘University of Illinois’ ውስጥ ፕሮፌሰር የሆኑትን - ዶ/ር ዴቪድ ስቶቨል (Dr. David Stovall)ን ያካተተ-ነው። ሙዚቃ፣ በጥቁር አልበረርባይነት ውስጥ የሚጫወተው ሚና፤ ከሌሎች ተከታታይ የሆኑ በስብሰባ አዳራሾች ከሚደረጉ ርዕሶች አንዱ-ክፍል ነው።

ግሮስ (Gross) እንዳሉት፤ ያለፈውን እውቅና ሳይሰጡ፣ ወደ ፊት መጓዝ አይቻልም። “ከቀድሞ-ሁኔታዎች መማር፣ ወደፊት የሚፈጠሩ ስህተቶችን ለማስወገድ እና ማህበረሰቡን የበለጠ አዎንታዊ-በሆነ አቅጣጫዎች ለመምራት ያስችላሉ፡” በኦክቶበር (October) ወር ውስጥ፤ ‘BSU’፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ - በመታሰቢያ ፕሮጀክት (Alexandria City Remembrance Project (ACRP) ውስጥ - የእኩልነት ፍትሃዊነት ተነሳሽነት ብሄራዊ የመታሰቢያ - ለሰላም እና ለፍትህ (Equal Justice Initiative’s National Memorial for Peace and Justice) የአከባበር-ቀን እና፣ በአላባማ (Alabama) ውስጥ ታሪካዊውን ሚውዚየም - አብሮ-ተቀላቅሏል። የአሌክሳንድርያ ሁለት የታወቁ ተጠቂ-የነበሩ - ጆሴፍ ማክሮይ (Joseph McCoy) እና ቤንጃሚን ታመስ (Benjamin Thomas) ህይወት-በምሳሌነት እንዲወክል - የተሰጠው አፈር/soil እዚያ-ነበር። ለተማሪዎች፤ ይህ ተሞክሮ - ጥልቅ-የሆነ ግንዛቤን በአሌክሳንድርያ ታሪክ ላይ እንዲያገኙ የረዳቸው እና በእኩልነት እና ሁሉን-አካታች የሆነ ጥምረን ፈጣሪ ሆኖ ሁሉን ተቀባይ የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚሰረገውን ስራ የሚያስታውስ -ሆኖ የሚያገለግል-ነው።

“በጣም-ትክክለኛ ከሆኑት መንገዶች ውስጥ አንዱ-የሆነውን - ተማሪዎች የበለጠ የማህበረሰብ ግንዛቤ፣ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚክ ኢ-ፍትሃዊነቶች የሆኑንብ በአሁኑ-ባለንበት ቀን ላይ - ሁለቱንም በቀድሞ-ጊዜ የነበሩትን የስኬት ድሎችን እና ስህተቶችን በማጥናት - ወደፊትን ለማሻሻል በሚረዳን መንገዶች ያለንበትን የአሁኑን-ጊዜ ለመቅረጽ እንዲያስችል የማድረግ ሃሳብን እንዲገፉበት እፈልጋለሁ፤” ብለው ገልጸዋል፣ ራ አሊም ሻባዝ (Ra Alim Shabazz)፣ የ‘BSU’ የሥራተኛ አድቫይዘር እና የACHS የኅብረ ትምህርት አስተማሪ። ሻባዝ (Shabazz) ጨምረውም፤ “ታሪክ አስፈላጊ-ሆኖ ሊገኝ-የሚችለው፣ ነፃነታችንን፣ ፍትህን እና ፍርሃዊ-ዕኩልነት ለሁሉም፤ የሚሉትን-ሊያረጋግጥልን የሚችለውን ጥሩ-የሆኑትን መንገዶች ለመግለጽ እንዲችል ስናደርገው ነው።”

ዛሬ ስላለው አመራርነት ምልከታ-በምናደግ ጊዜ - ብለው ግሮስ (Gross) ሲናገሩ፤ ታዳጊ ሰዎች በጥቁር ማህበረሰቡ ውስጥ - አትሌቶችን፣ አርቲስቶችን፣ የፖለቲካ ሰዎችን እና ሌሎች ታዋቂ-ሰዎችን ሊመለከቱ-ይችላሉ፤ ነገር ግን ተማሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተጽዕኖ ሊያገኙ የሚችሉት በትምህርት-ሰጪዎች - አስተዳደሮችን እና አሰልጣኞችን ጨምሮ እንደሆነ አጠንክረው ያምናሉ። “ትምህርት-ሰጪዎች - ተማሪዎች ያላቸውን ነጸብራቅነት እንዲመለከቱ መስታወቶችን ያቀርባሉ።”

# ACPS - ዶ/ር ኤሪክ ኮልማን (Dr. Eric Coleman)ን - እንደ የትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች (School Nutrition Services) ዳይሬክተር አድርጎ-እንኳን ደህና መጡ ብሏቸዋል



ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ኮልማን (Dr. Eric K. Coleman)፤ ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - እንደ አዲስ የትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች (School Nutrition Services (SNS) ሆነው በፌብሩዋሪ (Feb.) 6 ቀን 2023 ላይ ስራቸውን-ወስደዋል። የስራ-ድርሻቸውን በመውሰድ ላይ፤ ዶ/ር ኮልማን (Dr. Coleman) - የACPS የምግብ ፕሮግራም - የተመጣጠነ እና ጣፋጭ ምግቦችን - ስብጥር-ያላቸውን ባህሎችን፣ የጣዕም-አመራረጥ እና የአመጋገብ ፍላጎቶችን ከግምት-ውስጥ ባስገባ መልኩ - ከ15,000 በላይ ለሚሆኑ የክፍላችን/division ተማሪዎች፤ ማቅረብ-መቻሉን የሚያረጋግጡ ይሆናል። በተጨማሪም፤ በACPS የትምህርት ቤት የአመጋገብ ቢሮ ውስጥ ለሚኖሩ-ሁሉም ክንውኖች የቁጥጥር እና የአስተዳደራዊ ኃላፊነትንም ይወስዳሉ። ይህ የሚያካትተው፤ የዕቅድ-አወጣጥ፣ ማስተባበር፣ መቆጣጠር እና በሁሉም እንቅስቃሴዎች እና ሠራተኞች - በSNS ውስጥ - ግምገማ-ማድረግን ያካተተ-ነው።

"ዶ/ር ኮልማን (Dr. Coleman)ን ወደ ተቋማት እና ክንውኖች/Facilities and Operations መምሪያ - እንደ የትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች (School Nutrition Services) ዳይሬክተር ሆነው እንኳን-ደህና መጡ፤ ስል ደስታ-ይሰማኛል፤" ብለዋል፣ የACPS የተቋማት እና ክንውኖች/Facilities and Operations ዋና ሹም - ዶ/ር አሊሲያ ሃርት (Dr. Alicia Hart)። "በምግብ-ስራ አርትስ/culinary arts ያላቸው ሙያዊ-ብቃት፣ እንዲሁም በትምህርት ቤት የአመጋገብ ክንውኖች ውስጥ ባላቸው የረጅም ጊዜ ልምድ፣ ለትምህርት ቤት የአመጋገብ ቢሮ - ጤናማ እና የተመጣጠነ ምግቦችን ለተማሪዎቻችን ለማቅረብ ያለውን ግብ ለማሳካት ባለው ቀጣይነት ላይ ይረዳሉ።"

ዶ/ር ኮልማን (Dr. Coleman)፤ የ'U.S. Navy' ቬተራን/veteran ናቸው። ከK-12 ትምህርት ውስጥ ከዚህ በፊት የነበራቸው ልምድ - ክልላዊ የክንውኖች አስተዳዳሪ ሆነው በኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቢሮ - ለምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎቶች መስራታቸውን ጨምሮ - ልምድ-አላቸው። በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በዊትል (Whittle) ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ለምግብ ጥቅም ትምህርት እና ለልዩ ፕሮጀክቶች (Food Literacy and Special Projects)፣ ሲኒየር/senior የክንውኖች ዳይሬክተር ነበሩ።

ዶ/ር ኮልማን (Dr. Coleman)፤ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በትምህርት-አመራርነት ያገኙ ሲሆን፣ የማስተርስ ዲግሪን በትምህርታዊ ስልጠና እነ የንግድ አስተዳደር እና የባችለር ዲግሪን በንግድ አስተዳደር እና ዓለም-አቀፍ የአርቦች-ሰንሰለት ክትትል ክንውኖች (global supply chain operation) አግኝተዋል። ከምግብ አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆነ በእንግዳ-ተቀባይነት ኢንደስትሪ ውስጥ ከ20 ዓመታት በላይ ልምድ አላቸው፤ እና በ'American Culinary Federation' ብቁነትን ያገኙ ሼፍ/chef ናቸው። የብሄራዊ የአመራርነት እና ስኬት ማህበር (National Society of Leadership and Success) አባልም-ናቸው።

## ‘ACHS’፣ ክርስተፈር ስፔች (Christopher Speich)ን - እንደ የካምፓስ አስተዳደር አድርጎ አስተዋውቋል



ክርስተፈር ስፔች (Christopher Speich) - በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ፣ በረዳትነት የስራ-ድርሻ በዚሁ የስራ-ምድብ ላይ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ - ከጄንዋሪ (Jan.) 17 ቀን 2023 ጀምሮ፣ የካምፓስ አስተዳደር በሆነው የስራ-ድርሻቸው - ጀምረዋል። እንደ የካምፓስ አስተደደርነታቸው፤ ስፔች (Speich) - በዋና ርዕሰ መምህርነት - የ‘Connected High School Network (CHSN)’ን በመምራት የሚሰሩ ይሆናል። የዚህ የስራ-ድርሻ ኃላፊነቶች የሚያካትተው፤ የትምህርት-አሰጣጥ ፕሮግራሞችን ማስፈጸም፣ ከክፍሉ ድንጋጌ ጋር የስርዓተ-ትምህርት ዲዛይኑ ጎን-ለጎን ሆኖ መስራቱን ማረጋገጥ፣ እና የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታው ለሁሉም ተማሪዎች ስኬት ለማስገኘት ቀዳሚነት ይዞ መሰጠቱን መገምገምን ያካትታል። የካምፓስ አስተዳደሩ፤ በተጨማሪም - የዕለት-ተዕለት የካምፓሱን ክንውኖች ከሌሎች የ‘CHSN’ ካምፓሶች ጋር ትብብር-በማድረግ መምራትንም-ያከናውናል።

“ሚ/ር ስፔች (Speich) በኪንግ-ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) በሆነ የACHS ውስጥ - እንደ የካምፓስ አስተዳደር ሆነው - ዋና መሪ በመሆናቸው በጣም ደስ-ብሎኛል፤” ብለዋል የACHS ዋና ርዕሰ መምህር - ፒተር ባላስ (Peter Balas)። “የአመራርነት ልምዳቸው፤ ከተማሪዎች ጋር እና ከሠራተኞች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች፣ እንዲሁም በአጠቃላይ በቀለም-ትምህርት የላቀ ደረጃ ላይ በማድረስ ባለቸው ቁርጠኝነት ላይ በመስራታቸው፤ ለዚህ የ‘ACHS’፣ ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) ቦታ ትክክለኛ-ሰው ያደርጋቸዋል። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት ላይ በቀጣይነት መስራታችንን እየቀጠልን-ባለንበት ጊዜ፣ እና ለቲታኖቻችን የተጣራ ፈጠራዊ የሆነ የከፍተኛ ደረጃ ተሞክሮ እንዲኖአቸው በምናሳድግ ጊዜ፤ ከሚ/ር ስፔች (Speich) ጋር አብሮ-ለመስራት በጉጉት-እጠባበቃለሁ።”

ስፔች (Speich)፤ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - በሜይ (May) 2011 ላይ ተቀላቅለው-ነበር። በACHS ውስጥ፣ ከ2021 ጀምሮ - በልዩ-ሁኔታ የሚሰጥ (Specialized) የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ በዋና አስተዳደርነት ሲያገለግል የቆየ ነው። ይህን የስራ-ቦታ ከመያሱ አስቀድሞ፤ ስፔች (Speich) - በACPS ውስጥ እንደ ረዳት ርዕሰ መምህር፣ የተማሪዎች ዲን (dean)፣ አስተማሪ እና አሰልጣኝ ሆኖ ሰርቷል። ከጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ፣ እና ከሬድፎርድ ዩኒቨርስቲ፤ ዲግሪዎችን ይዟል።

# የትምህርት ቤት ቦርድ፣ ለ2023-24 የትምህርት ዓመት፣ የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታ በጀትን አጽድቋል




የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 ስብሰባው ላይ፣ ለ2023-24 የትምህርት ዓመት የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታዎች በጀት የሆነውን - $359.9 ሚሊዮን ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ለማጽደቅ ድምፅ-ሰጥቷል። ይህ በጀት - በሠራተኛ የማካካሻ-ክፍያ እና ለእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner) የትምህርት-አሰጣጥ ክፍት-ቦታዎች፣ ከK-4 ክፍሎች የማንበብና-መፃፍ፣ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሂሳብ፣ የትምህርት ቤት የጥበቃ-አገልብሎቶች፣ እና ለአትሌቲክ ፕሮግራም ዕቅድ እና እርዳታዎችን ለማሳደግ ትኩረት-ያደርጋል። የገንዘብ-እርዳታው- አዲስ የሆነውን የዳግለስ ማክአርተር (Douglas MacArthur) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን በኦገስት (August) 2023 ላይ ለመክፈት፣ የ1703 N. Beauregard St. ህንፃን እንደ-ጊዜያዊ ቦታ አድርጎ ለወደፊት የዘመናዊነት ማሻሻያ ፕሮግራሞች እንዲያገለግል እና የመከላከያ-የጥገና ስራዎችን በሌሎች የACPS ተቋማት ለማድረግንም ያካትታል።

“በዚህ ዓመት በጀት ውስጥ - አስፈላጊ-የሆኑትን እና የትምህርት ቤት ቦርዱ ቅድሚያ በመስጠት ከግምት-ውስጥ በሚያስገባቸው-ነገሮች ላይ እየሰራ-ባለበት ጊዜ፤ አስተያየታቸውን ላጋሩን የማህበረሰብ አባላቶች፣ ሠራተኞች እና ተማሪዎች - ምስጋናችንን ማቅረብ-እንፈልጋለን” ብለዋል የቦርዱ ሊቀመንበር ሜጋል ኤል አልደርተን (Meagan L. Alderton)። “በእያንዳንዱ ዓመት አዲስ-በጀት በምንቀርጽበት ጊዜ፤ በርካታ የሆኑ ጽምጾችን ማዳመጥ እና ከጊዜያዊ ጠቅላይ ስራአስኪያጅ-ጋር፣ የትምህርት ቤት ክፍል/division ሠራተኞች እና በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ ተጓደኞቻችን ከሆኑት ጋር በትብብር -መስራታችን በጣም እንዴት-አስፈላጊ እንደሆነ ማመስገን እንፈልጋለን። በዚህ የበጀት ሂደት ወቅት፤ ተማሪዎቻችን የላቀ-ደረጃ ያላቸው አስተማሪዎች እንዳላቸው ለማረጋገጥ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ለመበልጸግ የሚያስችላቸው የመረጃ-ምንጮች እና ለምርቃት ዝግጁ-ሆነው ለኮሌጅ፣ የስራ-መስኮች እና ለሕይወት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አብረን-እንሰራለን።”

ጊዜያዊ-ጠቅላይ ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) - ለትምህርት ቤት ቦርዱ -በጄንዋሪ (Jan.) 5 ቀን 2023 ላይ፣ እንዲቀርብ-የታሰበውን በጀት አቅርበው-ነበር። ለ2023-24 የACPS የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታ በጀት (The Proposed Combined Funds Budget) የሆነው- ይኸውን የማከናወኛ በጀትን ጨምሮ የያዘው፤ ተጨማሪ የትምህርት ቤት የአመጋገብ የገንዘብ-እርዳታዎች የሚሰጥ - እንዲሁም እርዳታዎች (grants) እና ልዩ የሆኑ ፕሮጀክቶችን የሚያቀርብ - በአጠቃላይ የ$359.9 ሚሊዮን በጀት ነው። ለ2023-24፣ የACPS - የክንውን-ማካሄጃ በጀት የሆነው $359.9 ሚሊዮን - ካለፈው ዓመት በጀት - በ4.2% ከፍ-ያለ ነው።

ይህ በጀት፤ የተቀጣሪ-ሠራተኞች ደሞዝና ጥቅማ-ጥቅሞችን በማሻሻል መፍትሄ-ሊያስገኝ እንዲችል በመሆን የተካተተ ሲሆን፣ ከፍተኛ-ጥራት ያለው ሠራተኛን፣ ጠብቆ-ማቆየትና ለመቅጠር - በኖርዘን-ቨርጅኒያ ያለውን የተወዳዳሪነት ደረጃን ACPS-መጠበቅ እንዲችል ያደርገዋል። እነዚህ እርምጃዎች የሚያካትቱት፤ በበጀቱ ላይ አማካኝ-ደረጃ የሆነው የ2.63% የደረጃ ጭማሪን ብቁ-ለሆኑ ተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ተጨማሪ የ3.0% ጭማሪ ለገበያ-ውድነት ደረጃ ማስተካከያ (market rate adjustment (MRA) - ብቁ-ለሆኑ ተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ከ1.25% እስከ 4.4% በሚደርስ-ደረጃ - ቀስ-በቀስ ጭማሪ የሚደግበት ቀጣይነት ያለው የገንዘብ እገዛ ጭማሪ በMRA ለተመረጡ ተቀጣሪ ሠራተኛ ቡድኖች፣ የ3% የማበረታቻ ጭማሪ (bonus) ብቁ-ለሆኑ ተቀጣሪ-ሠራተኞች የ “Top of Scale” ጭማሪ፣ በ“Hold-Step” ላይ ለሚገኙ እና መጠነኛ የጤና እንክብካቤ ጥቅማ-ጥቅሞች ጭማሪ ለህክምና፣ የዐይን እና ጥርስ-ህክምና

መሸፈኛ ክፍያዎችን ያካትታሉ። የገንዘብ-ስብስቡ (Funding)፣ ለጠበቃ እና ለሠራተኛ የመደራደሪያ ክፍያዎች - ለመጪው በማህበር የተቀጣሪ ሠራተኞች ቡድኖች መደረደሪያ-ንግግር ላይ እንዲውሉን የሚያካትት-ይሆናል።

የጸደቀው-በጀት፣ ለትምህርት አሰጣጥ እርዳታዎች - በዚሁ የትምህርት ክፍል ውስጥ - አዲስ የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner) የስራ-ቦታዎችን በማካተት እና ከእከK-4 ክፍሎች የማንበብና/መፃፍን ማሳደጊያ እርዳታ፣ እና ለሂሳብ ትምህርት አሰጣጥም በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ውስጥ የሚጨምር-ነው። በተጨማሪም፤ እነዚህ የገንዘብ-እርዳታዎች - ተጨማሪ የተማሪ እርዳታዎች ቡድን (Student Support Team) የስራ-ቦታዎችን ለመጨመር (የትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ የስነ-ልቦና ሙያተኞች፣ የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ መጠቀም ካውንስለር) ከተማሪ ማህበራዊ-ስሜታዊነት ፍላጎቶች-ጋር ሊረዱ የሚችሉ ለመጨመር-ያስችላል። ተጨማሪ የገንዘብ-እርዳታ ለACPS የአትሌቲክስ ፕሮግራሞች - ወደ የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት የአትሌቲክስ እና እርዳታዎችን ለተማሪ አትሌቶች ለማቀድ እና ለማስፋፋት ይውላል።

“የFY 2024 - የተጣመረ የገንዘብ እርዳታ በጀት - ቅድሚያ-የሚሰጠው፣ ለሠራተኞቻችን፣ ተቋሞቻችን እና የቀለም-ትምህርት እና የማህበራዊ-ስሜታዊ የመረጃ-ምንጮችን - ለተማሪዎች በማቅረብ ላይ ነው፤” ብለዋል የፋይናንስ ዋና ሹም ዶሚኒክ ተርነር (Dominic Turner)። “ይህ በጀት - የትምህርት ቤት ክፍላችንን/division - ጥራት-ያላቸውን አስተማሪዎችን ሠራተኞች ጠብቆ-ለማቆየት፣ እና ተወዳዳሪነት ባለው የስራ-ገበያ ላይ እጩዎችን በስኬት ለመቅጠር - የአስተማሪዎችን ክፍያ በማሳደግ እና ከፍተኛ-ጥራት ያለው የጤና እንክብካቤ ጥቅማ-ጥቅሞችን ማቅረብን-በመቀጠል - ቦታውን-ጠብቆ ይሠራል። በሚቀጥለው በልግ (fall) አዲስ ትምህርት ቤትን ለመክፈት እና ለወደፊት የትምህርት ቤት የዘመናዊነት-ፕሮጀክቶች ስራችንን-ለማጎልበት በምናደርገው ስራ-ደስተኞች ነን።”

አዲስ የገንዘብ-እርዳታው፤ ለተቋማት እና ከንውኖች - የትምህርት ቤት የጥበቃ-አገልግሎቶችን፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የመከላከያ እድሳት እና ጥገናዎች ለማመቆያ/heating፣ አየር ማናፈሻ/ventilation እና ለማቀዝቀዣ ዘዴዎች (air conditioning systems (HVAC) ያካተተ-ሆኖ ይሠራል። ACPS - የኬሬ-ሜትር የትምህርት ቤት ተቋማት ስፋትን በማሳደግ፣ ተጨማሪ በሆነ የገንዘብ እርዳታ ለተማሪዎች አዲስ ትምህርት ቤትን በኦገስት (August) 2023–የዳግለስ ማክአርተር (Douglas MacArthur) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ለመክፈት፤ ከህንፃ መሃንዲስ ጋር እና ከተጨማሪ የቨርጅኒያ የቅድመ-ትምህርት ቤት ተነሳሽነት (Virginia Preschool Initiative (VPI) የመማሪያ-ክፍሎች ጋር– እና በአዲስነት የተገዛውን የ1703 N. Beauregard St. ህንፃን - እንደ ጊዜያዊ-ቦታ አድርጎ በመጪው የዘመናዊነት ፕሮጀክቶች ጊዜ ለመጠቀም ነው።

“የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ ይህን የFY 2024 በጀት – ለተማሪዎቻችን-ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ፕሮግራሞችን እና እርዳታዎችን ለመስጠት የሚያችለውን በማጽደቁ፤ ምስጋናችንን ለማቅረብ-እንፈልጋለን። ይህ በእውነት የሚያመለክተው - በሠራተኞች፣ የተማሪ የመረጃ-ምንጮች እና በተቋማት ላይ ኢንቬስት እንደተደረገ እና ዓላማችንን እና ራዕያችንን ወደሆነው እኩልነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ተማሪዎቻችን በማቅረብ ላይ ወደፊት-እንድንገባ የሚያደርገን ነው፤” ብለዋል ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)። “እንዲሁም ለፋይናንስ ሹም ለሆኑት ዶሚኒክ ተርነር (Dominic Turner) እና ለክፍሉ-ቡድን ሠራተኞች - በዚህ በጀት ላይ ለመስራት፣ መረጃዎችን ለማጋራት እና አዲስና-ማሻሻያዎች (updates) እና በሂደቱ-ወቅት ሙሉ ለጥያቄዎች መልስ-በመስጠት ላሳዩት ትጋት - ምስጋናችን-ይድረሳሁ።”

ከዚህ የቁርጠኝነት ስራ ጋር አብሮ በመስራት - የዘር እኩልነትን በሁሉም የውሳኔ-አሰጣጡ መሐል-ልብ ውስጥ ለማስቀመጥ፤ የትምህርት ቤቱ ቦርድ፣ የ2025 ስልታዊ ዕቅድ (2025 Strategic Plan) - የማስፈጸም ስራ ላይ እና ቀጣይነት ባለው ትኩረቶች ላይ እርዳታዎችን የሚያደርገውን በጀት አጽድቋል። ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity for All)። የበጀት ሂደቱ አጠቃላይ መግለጫው፣ እና የጊዜ-አቀማመጡ - በ[ACPS Budget ድህረ-ገጽ] ላይ እንዲሁም፣ በ[ACPS FY 2024 Proposed Budget Book] ላይ መገኘት-ይችላል።

በበጀት አሰራር ሂደቱ ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማመቻቸት፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ በተጣመረ የገንዘብ እርዳታ በጀት ላይ ሦስት የስራ ክፍለ-ጊዜዎችን በዚህ-ሂደት ላይ እና ያካሄደውን የሕዝብ-ተሰሚነት (Public Hearing) በጃንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 ላይ አድርጎ-ነበር። [ሁሉም የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባዎች እና የስራ ክፍለ-ጊዜዎች - በኦንላይን ላይ ሊታዩ-ይችላሉ]። የከተማው ምክር ቤት፣ በጀቱን ለመጪው ዓመት፣ ለACPS የተመደበውን ጨምሮ፣ በሜይ (May) 3 ቀን 2023 ላይ በስራ-ላይ የሚያውል-ይሆናል።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ከ15,700 ተማሪዎች በላይ - ከ119 ሃገራት የመጡትን እና 124 ቋንቋዎችን የሚናገሩትን እያገለገለ-ነው። ACPS፤ 18 ትምህርት ቤቶች ያሉት፤ ሁለት መካከለኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ሁለት ከK-8 ትምህርት ቤቶች፣ አንድ pre-K ትምህርት ቤት እና - በዓለም-አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አለው። ACPS፤ የዘር እኩልነትን በሁሉም ውሳኔዎች መሃከል-ላይ አድርጎ በቁርጠኝነት-የሚሰራ እና እያንዳንዱ እና ሁሉም ተማሪ ስኬታማ-እንዲሆን ለማረጋገጥ የሚሰራ-ነው። www.acps.k12.va.usን ጎብኙ።

## በቅርቡ-የሚከናወን: የጦር-መሣሪያ መመርመሪያ መሣሪያ የዳሰሳ-ጥናት




የማህበረሰብ ተሳትፎ የዳሰሳ-ጥናት፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 24 ቀን 2023 ላይ የሚከፈት-እና የጦር-መሣሪያ መመርመሪያ መሣሪያን በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የመጠቀም-ሁኔታዎችን ከግምት-ውስጥ የሚያስገባ-ነው። የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - በፌብሩዋሪ (Feb.) 2 ቀን 2023 ላይ ባካሄደው ስብሰባው ላይ፣ በማህበረሰብ ተሳትፎ የዳሰሳ-ጥናቱ ለመቀጠል አጽድቋል።

“በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ - የጦር-መሣሪያ መመርመሪያ መሣሪያን መጠቀም፣ መሣሪያዎች ወደ ትምህርት ቤት ተቋማቶቻችን የመግባት-ሁኔታውን ለመቀነስ የሚያስችል-ይሆናል፤” ብለዋል - የተቋማት እና የክንውኖች ሹም፣ ዶ/ር አሊሲአ ሃርት (Dr. Alicia Hart)። “በመጨረሻም፤ በአንድ-ተቋም ውስጥ የጦር-መሣሪያዎች የመገኘት-ዕድልን መቀነስ - (ለእኛ የጥበቃ-የአሰራር መንገድ) - ለተማሪዎቻችን ደህንነቱ-የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን ማቅረባችንን ለማረጋገጥ፤ አዎንታዊ የሆነ እርምጃ ነው።”

የማህበረሰብ ተሣትፎ የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰብ አባላቶች ክፍት-ይሆናል። ተጨማሪ መረጃዎች እና ወደ ዳሰሳ-ጥናቱ የሚወስደውን ማገናኛ/link ያካተተ መረጃ፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 24 ቀን 2023 - የ‘Express’ ዕትም ውስጥ ይካተታል።

## የACPS ቤተሰቦች፣ ወደ ኖርዘን ቨርጅኒያ የአደንዛዥ ዕፅ - የርቀት/Virtual ፓኔል ተጋብዘዋል




የ‘Northern Virginia Family Network (NVFN)’ እና ‘Formed Families Forward (FFF)’ - “ትምህርት ቤቶች ምላሽ-ስጡ/Schools Respond: ታዳጊ-ወጣቶች እና የአደንዛዥ ዕፅ፣ (Teens and Substance Abuse)፣ ከኖርዘን ቨርጅኒያ ትምህርት ቤቶች የተደረጉ-አዲስና ማሻሻያዎች (Updates from Northern Virginia Schools)” በሚል-ርዕስ - የርቀት ፓኔል

አቀራረብ (virtual panel presentation)ን ያካሂዳሉ። ይህ መረጃ-ሰጪ እና ጊዜውን-የጠበቀ ውይይት፣ ሮብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 22 ቀን 2023 ላይ፣ ከ7-8:30 p.m. ድረስ ይካሂዳል። ሁሉም ቤተሰቦች እንዲካፈሉ ይበረታታሉ።

ፓናሉ/panel፤ ከአካባቢ ትምህርት ቤቶች ወኪሎች - በአሁኑ-ጊዜ ስለአሉት አስቸጋሪ-ፈጣን-ነገሮች፣ እንዴት ምላሽ-እያገኙ እንደሆነ እና ቤተሰቦች እንዴት መርዳት እንደሚችሉ የሚያጋራ-መረጃዎችን ይሰጣል። ከፓናሊስቶቹ መካከል የሚካተቱት፤ የተማሪ እርዳታ ቡድኖች - ዋና ዳይሬክተር፣ ዶ/ር ቪክተር ማርቲን (Dr. Victor Martin) እና ከK-12 የአደንዛዥ ዕፅ መከላከያ & ጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶች ካውንስለር - ሩቲ መርካዶ (Ruthy Mercado)፣ ሁለቱም - የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)ን የሚወክሉ-ናቸው።

ፓናሉን በመምራት የሚያገለግሉት፤ የ 'National Alliance on Mental Illness Northern Virginia' ዋና ዳይሬክተር ሬበካ ካይስሊንግ (Rebecca Kiessling)፣ የ'FFF' ምክትል ዳይሬክተር ኒና ማንጋናሪስ (Nina Manganaris) ናቸው።

በhttps://bit.ly/NVFNsubstancepanel ላይ ተመዝገቡ።

## የ'ACPS'፤ የስራ-መስክ እና የቴክኒካል የትምህርት ፕሮግራሞች - ተማሪዎች ለስኬት ያዘጋጃል



የስራ-መስክ እና ቴክኒካል ትምህርት (Career and Technical Education (CTE) - ተማሪዎችን፣ ወደ ስራ-መስኮች እና ኮሌጅ የሚያሰናዳ-ነው። የ'CTE' ወር፣ የሚታሰበው በፌብሩዋሪ (February) ወር ውስጥ፣ ከ2023 ገጽታው-ከሆነው/theme - "Celebrate Today, Own Tomorrow" ከሚለው-ጋር ነው። 'CTE' ለተማሪዎች የስራ-መስክ ዝግጁ እንዲሆኑ እና ሃገራችን በኢኮኖሚያዊ ስኬት ያላት ሃገር እንድትሆን በሚያደርገው ወሳኝ-የሆነ ሚና ላይ ግንዛቤን ማሳደጊያ ጊዜ-ነው።

የ'CTE' ወር በሚታሰብበት ጊዜ፤ የአገረ-ግዢ ግሌን ያንግኪን (Governor Glenn Youngkin) የደነገገው፤ "የስራ-መስክ እና ቴክኒካል ትምህርት - በደንብ-ለተማረ የስራ-ኃይል ጠንካራ-መሠረት ነው - ይህም በኢንዱስትሪ ውስጥ ምርታማነትን ለማዳበር እና ለቨርጅኒያ በአለም-አቀፍ የንግድ-ስፍራ ላይ መሪነቷ እንዲቀጥል ያደርጋል" ብለዋል። በመጨምርም በማስታወሻነት ሲያስቀምጡ፤ "የስራ-መስክ እና ቴክኒካል ትምህርት - ለሕይወት ዘመን የሚዘልቅ የመማር ዕድሎችን የሚሰጥ ሆኖ፣ ግለሰቦች ወደ የበለጠ የስራ-መስክ ምርጫዎች፣ የተስፋፋ ክፍያ-የማግኘት ዕድልን፣ እና ትልቅ-የሆነ የስራ እርካታን እንዲያገኙ ያደርጋል።

'CTE'፣ ተማሪዎች - ወደ በርካታ የቀለም-ትምህርት እውቀት ለማመልከት አማራጮችን የሚሰጥ እና በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ ለሚያስፈልገው የስራ-ቦታ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኒካል ችሎታዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል። ተማሪዎች፤ በመካከለኛ-ደረጃ፣ በከፍተኛ ትምህርት ቤት እና በኮሌጅ ውስጥ ትምህርት-የሚሰጡባቸውን የኮርስ-ዓይነቶች ለመፈተሽ-ይችላሉ። ለበርካታ የስራ-መስክ አማራጮች - በራቸውን የከፈቱ፤ በርካታ በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ - የ'CTE' ዕድሎች አሉ። እነዚህም የሚያካትቱት: business and information technology, family and consumer sciences, health and medical sciences, Junior Reserve Officers' Training Corps (JROTC), marketing, technology education and trade and industrial fields - ናቸው።

ACPSም፣ የ‘CTE’ የቀለም-ትምህርቶች እና ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን፣ ይህም የሚያካትተው - የአገረ-ገዢው የጤና ሣይንሶች አካዳሚ (Governor’s Health Sciences Academy) እና የ‘STEM’ አካዳሚን ነው። ማመልከቻን-የማስገቢያ የመጨረሻ-ማብቂያ ቀን ሆኖ ለACPS academies and program ማመልከቻ የተቀመጠው-ቀን ማርች (March) 15 ቀን 2023 ነው።

ለኢንዱስትሪ ምስክርነትን የሚሰጡ - የትምህርት-አሰጣጥ ፕሮግራሞች እና ዕድሎች፣ ተማሪዎች የኮሌጅ- እና የስራ-መስክ ዝግጁነትን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ይህም በመማሪያ-ክፍል ውስጥ ያገኙት እውቀት - ለግማሽ-ሰዓት (part-time)፣ ክፍያ-ያለው ቅጥር እንዲያገኙ እና ለምርቃታቸው ክሬዲን እንዲሆናቸው ያስችላቸዋል።

የብሄራዊ ህብረት ለአጋርነቶች በፍትሃዊ-እኩለንት (The National Alliance for Partnerships in Equity)፤ በ2020-21 የትምህርት ዓመት ወቅት የሚከተሉትን አግኝቷል:

- 94% የቨርጅኒያ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ በ‘CTE’ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካፈሉት፤ ተመርቀዋል።
- 93% የ‘CTE’ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች - ከፍተኛ ደረጃ-በኋላ ፕሮግራም (post-program) ምደባን በቨርጅኒያ ውስጥ አግኝተዋል።
- 41% የቨርጅኒያ የ‘CTE’ የሁለተኛ-ደረጃ በኋላ (postsecondary) ተማሪዎች፤ ማረጋገጫ/credential፣ ሰርተፊኬት ወይም ዲግሪ አግኝተዋል።

‘CTE’ - ለሁለተኛ-ደረጃ እና ከሁለተኛ-ደረጃ በኋላ (postsecondary) ተማሪዎች፤ ከቀለም-ትምህርት እና የቴክኒካል ችሎታዎች ጋር እና በአሁኑ-ጊዜ እና ወደፊት ላለው የስራ-ኃይል ዝግጁ የሚያደርጋቸው እውቀትን ሰጥቷል። በፍትሃዊ-እኩነት ላይ - በፆታ፣ በዘር፣ በጎሣ፣ ያለውን-ክፍተት ስንዘጋ፤ ያለንን የንግድ፣ የኢኮኖሚ እና በሰብዓዊነት ላይ ልናገኛቸው-የምንችለውን መገንዘብ-እንችላለን።

ተጨማሪ መረጃዎች፤ ከ‘Virginia Association for Career and Technical Education’ ላይ መገኘት-ይችላሉ። ይህ ድርጅት - ለሁሉም የ‘CTE’ ገጽታዎች - በትምህርት እና በቨርጅኒያ ኮመንዌልዝ (Commonwealth of Virginia) ውስጥ በኢኮኖሚ ጥቅም-ለማስገኘት፤ ተጠሪ ተከራካሪ ሆኖ ይሠራል።  ሁሉንም የስራ-መስክ እና የቴክኒካል ትምህርት ዕድሎችን በማክበር-ላይ የሚከተለውን-በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በመጠቀም አብራችሁን ተካፈሉ፤ #CTEMonth

## ‘ACPS’፣ የትምህርት ቤት ‘100 Days’ን፣ አክብሯል




የከፍተኛ ምዕራፍ (milestone) የትምህርት ቤት 100ኛ ቀን፤ በ17 የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ - በፌብሩዋሪ (Feb.) 13 ቀን 2023 ላይ ተከብሮ-ነበር። ቀኑ፤ ተማሪዎች ስለአገኟቸው ውጤቶች ለማሰብ ዕድል የሚሰጣቸው እና እንዲሁም ስለ ወደፊት የመማር እድሎች በጉጉት እንዲጠባበቁም የሚያደርጋቸው-ነው።

የመማሪያ-ክፍል አከባበሮች እንደየክፍል-ደረጃው የተለያየ እና የሂሳብ እና የስፔሊንግ/spelling ችሎታዎችን፣ የ‘STEM’ እንቅስቃሴዎች እና ጽሁፍን-የማበረታታት ልምምዶችን አካቷል። አንዳንድ የነበሩ አስደሳች-ሁኔታዎችን በሚከተሉት-ላይ ተመልከቱ፤ #ACPS100thDay posts on Facebook, Twitter እና Instagram.

የተስተካከለ የቀለም ትምህርት የቀን-መቁጠሪያን የሚከተለው - ሣሙኤል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት - በዓሉን በጄንዋሪ (Jan.) 30 ቀን 2023 ላይ አክብሮ-ነበር።

በፌብሩዋሪ (February) ወር ሙሉ ከሚካሄዱት የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች ጋር - የትምህርት ቤት 100ኛ ቀን (100th day of school)፣ ለአስተማሪዎች - ስለተማሪያቸው የእድገት-ሂደት ለመመልከት ጊዜ የሚያገኙበትም-ነው። ይህ - የዓመቱ-አጋማሽ ምልከታ-የማድረጊያ ጊዜ፤ ተማሪዎች ወደ ግባቸው እንዲደርሱ በትክክለኛው-መንገድ ላይ እንዲቆዩ የሚረዳ-ነው።

## የፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ (SUMMARY)



ስብሰባው - በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ - ለ2023-24 የትምህርት ዓመት የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታዎች በጀት የሆነውን - $359.9 ሚሊዮን ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ለማጽደቅ ድምፅ-ሰጥቷል።

የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ር ዕሶች ምላሽ-ሰጥቶበትም ነበር:

- አዲስና-ማሻሻያ (Update)፣ የጦር-መሳሪያዎችን የመቀነስ ፓይለት (Weapons Abatement Pilot) ሃሳብ-የቀረበበት
- የፖሊሲ ክለሳዎች (Policy Revisions)
- የትምህርት ቤት የሕግ-ማስከበር አጋርነት (School Law Enforcement Partnership (SLEP) ላይ የቀረቡ-ሃሳቦች፣ አስተያየት እና የሠራተኛ ማስታወሻዎች
- SY22-23 ትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ የመረጃ-ስብስብ/Data (Q1 እና Q2)
- የክልል-ወሰን ትንተና (Boundary Analysis)

በተጨማሪም፤ አዲስ ቪዲዮ - በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 ላይ ተጋርቶ-ነበር፤ ስብሰባው በእይታ-ያቀረበው - የትምህርት ቤት ቦርድ አባል የሆኑት ዶ/ር ሚሼል ሪፍ (Dr. Michelle Rief)፣ ባለን ስልታዊ ግብ መሠረት አድርጎ - ማግኘት-መቻልን እና እርዳታን - ለሁሉንም ተማሪዎች ለማረጋገጥ - በእኩልነት የማግኘት እና ከፕሮግራሞች ጋር ተሳትፎ-ለማድረግ እና በመማር ላይ ያሉትን እንቅፋቶች ለመቀነስ እርዳታ ማድረግን ላይ ምላሽ-የሰጡበት ነው። ይህ ቪዲዮ፣ በቅርብ-ጊዜ ያለውን የ'School Board vignettes' ተከታታይ-ክፍልን - ስለ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና ማህበረሰብ አባላቶች - ከትምህርት ቤት ቦርድ ስራዎቹ - ከውስጣዊ ምልከታዎች ጋር፣ ክፍሉ/division በዓላማው፣ ራዕዩ እና ግቦቹ ላይ ያለውን - ለሕይወት ያለውን የስልታዊ ዕቅድ ጋር እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ-ነው። ከዚህ-ቀደም የነበሩ በዚህ-ተከታታይ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት - የሚያካትተው:

- የጄንዋሪ (Jan.) 20 ቀን 2023 ቪዲዮ የሚያሳየው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ ሊቀ-መንበር - ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton) ሁሉም ተማሪዎች ማግኘት ወደሚችሉ እና ከፍተኛ-ጥራት ወዳለው የትምህርት አሰጣጥ እንዲሳተፉ ወደሚያደርጋቸው - , የትምህርት-አሰጣጥ የላቀ-ደረጃ ያለው ስልታዊ ግባችን የሚያወያየውን የሚያሳየውን አቅርቧል።
- የዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 ቪዲዮ የሚያሳየውን - የትምህርት ቤት ቦርዱ አባል ታሚ ኢግናቺኦ (Tammy Ignacio) በ2022-23 ACPS ዋናው-ትኩርት ከሚያደርግባቸው ዙሪያዎችን አንዱ ስለሆነው፣ ስለ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና

[የቀለም ትምህርት መማር መልሶ-ማቋቋሚያ (social, emotional and academic learning recovery (SEAL)፣ መግለጫ ሲያደርጉ](#) ለእይታ-አቅርቧል።

- የኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 ቪዲዮ ያቀረበው - የትምህርት ቤት ቦርድ አባል ኬሊ ካርማይክል ቡዝ (Kelly Carmichael Booz) የACPS 2025: Equity for All Strategic Plan's - ስልታዊ ግቦችን በዘዴያዊ አቀማመጥ ላይ የሚወያየውን - አቅርቧል።
- የኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 ቪዲዮ-የሚያሳየው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ አባል፣ አብደል-ራህማን ኤልኖቢ (Abdel-Rahman Elnoubi) - ወደ በጀት-ሂደቱ ውስጥ ወደውስጥ-ዘልቆ በማሳየት የሚያቀርበውን አሳይቷል።
- የሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 ቪዲዮ የሚያሳየው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ ሊቀ-መንበር - ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton) - የስልታዊ ዕቅድ (strategic plan)ን በአጠቃላይ ራዕይ፣ ዓላማ፣ እና ዋና እሴቶች የሚያሳየውን የሚያጋራ-ሲሆን፤ እና እንዴት - ከውስጣዊ-ልቡ ጋር ያለውን ከዘር-እኩልነት ጋር የሚገናው - የ'Equity for All 2025 Strategic Plan' ሊለወጥ-እንደሚችል አሳይቷል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘትም ትችላላችሁ።

## በፌብሩዋሪ (Feb.) 9 ቀን 2023 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ፌብሩዋሪ (Feb.) 9 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 75.90 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በፌብሩዋሪ (Feb.) 9 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።